፮/ ለልምምድ ተማሪዎችን ከሚልኩ የግልና የመንግስት ተቋማት በውስጥ ደንቡ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ፤ ሌሎች አገልግሎቶቹን የመሸጥ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አገልግሎትን የመግዛት፤

፯/ የህብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ የህክምና አገልግሎቱን ክፍያ የመወሰን፤ የነጻ ህክምና ተጠቃሚዎች መለየት የሚያስችል ወጤታማ አሰራርን የመቀየስ፤

፰/ መደበኛውን የህክምና ቅብብሎሽ ሥርዓት ሳይከተል ለሚመጣ ታማሚ ልዩ ክፍያ በማስከፈል የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚደረግበትን ሥርዓት የማመቻቸት፤

፱/ ሠራተኞችና ተማሪዎች ስለሚያገኙት የህክምና አገልግሎት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የመወሰን፤

፲/ ሴሚናሮች፣ ዓውደ ጥናቶችና ሲምፖዚየሞችን የማዘጋጀት፤

፲፩/ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት የመመስረትና እንደአስፈላጊነቱ ጥምረት የመፍጠር፤

፲፪/ የማማከር፣ የሥልጠናና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የመስጠት፤

፲፫/ የትምህርት መጽሔቶችና ጋዜጦችን ማቋቋምና በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የማሰራጨት፤

፲፬/ ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

## ፮. ነፃነትና ተጠያቂነት

፩/ ኮሌጁ በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ የተደነገገው የአስተዳደር ነጻነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከተመለከተው ተጠያቂነት ጋር ይኖረዋል፡፡

፪/ ኮሌጁ ተልዕኮውን በሚገባ ስለማሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያቂነት ይኖርበታል፦

ሀ) በመማር ማስተማርና የምርምር ሥራዎቹ ለመንግሥት ፕሮግራሞች ቅድሚያ መስጠቱንና ከሃገራዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን፤

ለ) አጠቃላይ አሠራሩ በግልጽነትና በአሳታፊነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን፤

ሐ) የበጀትና ሃብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢና ለህዝብ ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ መሆኑን፤

መ) የመማር ማስተማር፣ የምርምር ሥራዎች እና የህክምና አገልግሎቶች ተቋማዊ ሆነው በግልጽ የሚከናወኑ መሆኑን፤

ሠ) ኮሌጁ በሚያስመዘግበው የጥራትና ተገቢነት ውጤት የሚለካ መሆኑን፡፡

6/ charge, in accordance with its rules service fees from practicing students of other private and public institutions; sell other services and, where necessary, buy services;

7/ determine medical service fees with due consideration of the financial capability of the public, and design effective mechanisms for identifying beneficiaries of free medical services;

8/ establish a system for rendering service, by charging extra fee, to patients who bypass the conventional referral system;

9/ determine the free medical service available to its students and staffs;

10/ organize seminars, workshops and symposiums;

11/ establish partnership with domestic and foreign higher education institutions, research institutions and other organizations having similar objectives and, where necessary, establish consortium;

12/ provide consultancy, training and other related services;

13/ establish academic journals and newsletters and disseminate same through electronic or any other means;

14/ carryout such other related activities as are appropriate to attain its objectives.

## 6. Autonomy and Accountability

1/ The College shall enjoy the autonomy provided for under Article 17 of the Proclamation with the accountability provided for under sub-article (2) hereof.

2/ The College shall have accountability for fulfillment of its objectives and responsibilities, more specifically whether:

a) its academic and research activities give priorities to government programs and are relevant to the country's situations;

b) the performance of its activities are transparent and participatory;

c) its allocation and utilization of budget and resource are based on cost effectiveness and responsibility to the public;

d) its academic and research activities and medical services are institutionalized and are undertaken with transparency;

e) it is evaluated based on the quality and relevance of its achievements.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ኮሌጁ የውጪና የሀገር ውስጥ ተማሪዎችን የትምህርት ወጪ ክፍያ በማስከፈል ሊያስተምር ይችላል፡፡

## ፲፮. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፩፻፷፯/፪ሺ፩ ድንጋጌዎች ከዚህ ደንብ ጋር እስካል ተቃረኑ ድረስ የኮሌጁ ማስተማሪያ ሆስፒታልን በተመ ለከተ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ፲፯. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የቅዱስ ጳውሎስ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮሌጁ ተላልፈዋል፡፡

## ፲፰. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3/ Notwithstanding sub-article (2) of this Article, the College may admit foreign and local students with tuition fees.

## 16. Applicable Laws

The provisions of the Federal Hospitals Administration Council of Ministers Regulation No. 167/ 2009 shall, in so far as they are not inconsistent with this Regulation, be applicable with respect to the teaching hospital of the College.

## 17. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Saint Paul General Specialized Hospital are hereby transferred to the College.

## 18. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 30th day of March, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**